# የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ አገር-ወዳድና ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች እና ኢሕአዴግ፤ ከዚኽ ወዴት?

*ከአያል ሰው ደሴ፤ የግል አስተያየት*

## ***ክፍል አንድ***

### ሀ) አጠቃላይ፤

በዚኽ "የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ አገር-ወዳድና ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች እና ኢሕአዴግ፤ ከዚኽ ወዴት?" በሚል ርዕስ አጠቃላይ የአገራችንን የፖለቲካ ሁኔታ በተለይ ድኅረ-ምርጫ ሁለት-ሽህ-ሁለት ያለውን ጭብጥ በአጭሩ በመዳሰስ፣ ኢሕአዴግ በአንድ በኩል አገር-ውዳዱና ዴሞክራቱ ወገን በሌላ በኩል የሕዝባችንን የፍትኅ፣ የእኩልነትና የልማት እንዲሁም የአገራችንን አንድነት ጥያቄዎች እውን በማድረጉ ረገድ የሚኖራቸውን አዎንታዊና አሉታዊ ሚናዎች ለመቃኘትና በተለይም ለአዎንታዊ ለውጥ የቆመው ኃይል ከሚገኝበት የማይጥም ይዞታ ሊላቀቅና የሚጠበቅበትን ታሪካዊ ኃላፊነት ሊወጣ የሚችልበትን መንገድ ለመጠቆም እሞክራለሁ።
*(ከወዲሁ ለወገኖቼ በአክብሮት የምገልፀው ከአሁን በፊት ባቀረብኳቸው ረዘምዘም ያሉ መጣጥፎች ላይ ከብዙዎች የደረሱኝን አስተያየቶችና ሂሶች ሀሳቦት ውስጥ በማስገባትና ከምስጋና ጋር ከልብ በመቀበል ይኽ የግል አስተያየት በአንድ ጊዜ ከሦስት ገፆች ሳይበልጥ በተከታታይ እንደሚቀርብ ነው።)*

የኢትዮጵያ ሕዝብ ለፍትኅ፣ ለእኩልነትና ለአንድነት በልዩ ልዩ መልክና ፈርጅ የሚያደርገው ትግል የከፈለውንና እየከፈለ ያለውን መስዋዕትነት በሚመጥን ሁኔታ አርኪ ውጤት ባያስገኝም ትግሉ ቀጥሏል፤ ይቀጥላልም። ይሁንናም የታሰበውን ያኽል ውጤት ባይገኝም ሕዝባዊ ትግሉ በቀጠለ ቁጥር በዜጎች ላይ የተጫኑ ችግሮች እንዲበራከቱና ሥር እንዲሰዱ በር የሚከፍተውን ያኽል በአኳያው ለውጥ-ገርጋሪ ክፍሎች ወደዱም ጠሉም እያንዳንዱ የፍትጊያ ሂደት እየተዋቸው የሚያልፍ ለትግሉና ለሕዝብ ጠቀሜታ ያላቸው አዎንታዊ ገጽታዎች እንደሚኖሩ ሊታወቅ ይገባል። ቀደም ሲል በደርግ ግዛተ-ዘመን አብዛኛው ኢትዮጵያዊ የሚጠይቀውና የሚጠብቀው ደርግ እንዴት ይሻሻል ይሆን? ሣይሆን መቼ ይለወጥ ይሆን የሚል እንደነበር ሁሉ ሕወሓት/ኢሕአዴግ ማዕከላዊ የመንግሥት ሥልጣን ከተቆጣጠረበት ጊዜ አንስቶ በሥልጣን ላይ ለመቆየትም ይሁን ከአገዛዙ ፍልሥፍና በመነጨ በየጊዜው በሚፈጽማቸው ተግባራትና በሚከተላቸው ብሔራዊ ጥቅምን የማያስከብሩና የሕዝብን መብቶች በእጅጉ የሚፃረሩ መርኃ-ምሪቶች (ፖሊሲዎች) ምክንያት የሚስተዋለውም እንዲሁ ይኽ ሥርዓት ስለሚሻሻልበት ሣይሆን የቁጥረ-ብዙ ኢትዮጵያውያን ጥያቄና ጥባቆ መቼ ይወገድ ይሆን? የሚል እንደሆነ የብዙዎች ድምዳሜ ነው። እንዴት? ለሚለው ጥያቄ ግን አጥጋቢና ሰብሰብ ያለ ምላሽ ለመስጠት በፖለቲካው መስክ የተደራጁ ክፍሎች የተጨነቁበትና አሁንም እየደከሙበት ያለ ጉዳይ እንደሆነ ይታወቃል። ሆኖም እነዚኽ ኃይሎች ምላሹን በማፈላለጉ ረገድ የሚያደርጉት ልፋትና ድካም አገዛዙን መሥመር እንዲይዝ ከማስገደድም ይሁን ከማስወገድ ይልቅ ተጠምዝዞ እራሣቸውን እያደከማቸው መሆኑንም ያስተውሏል።

ስለዚኽ በአንድ በኩል ሕወሓት/ኢሕአዴግ እራሱን ሊያሻሽልና ሊለወጥ መቻል አለመቻሉን፣ በሌላ በኩል ያለው ሥርዓት ተቃዋሚና ለአዎንታዊ ለውጥ የቆመው ዴሞክራሲያዊው አማራጭ ኃይል በሕወሓት/ኢሕአዴግ የውስጥ መሻሻል ወይም መቀየር (መለወጥ) ላይ ያለው ወይም ሊኖረው የሚችለው አስተዋጽዖ፣ አቅምና ሚና፤ እንዲሁም እነዚኽ ሁለት ኃይሎች (ገዥው ፓርቲና ለለወጥ የቆመው አማራጭ ክፍል) አሁንም ሆነ ወደፊት የሚያደርጉት መሳሳብና ፍልሚያ ለአገራችንና ለሕዝባችን አዲስ ዴሞክራሲያዊና ፍትኃዊ ሥርዓትን እውን ከማድረጉ አኳያ የሚኖራቸው አዎንታዊና አሉታዊ አስተዋጽዖ፤ እና በመጨረሻም አንዱ በሌላው መቃብር ላይ ለመቆም ከማሰብ ውጭ ሁለቱም ተፃራሪ ክፍሎች መኻል ላይ ሊገናኙ የሚችሉበት ሁኔታ ሊኖር መቻል አለመቻሉ ከአጉል ምኞታዊነትም ሆነ ከቆየ የገረረ አንድ-ጎንዮሽ አስተሳሰብ በወጣ መልኩ የዛሬን ብቻ ሣይሆን የነገ ተነገ-ወዲያውን ባየና ብሔራዊ ጥቅምንና የሕዝብን ሉዓላዊነት ባስተባቃ መልኩ በተገቢና በእርጋታ ሊመረመርና ሊቃኝ የሚያስፈልግ ይመስለኛል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥያቄ መሠረታዊ የመብትና የኅልውና ጥያቄ ነው። ሕዝቡም ሁለንተናዊ መብቶቹ እስካልተከበሩለት ድረስ በቁጥ-ቁጥ በሚደረጉ መሸንገያዎችም ይሁን አንዳንድ ሁኔታዎችን ቀደም ሲል ከነበረው ደርጋዊ የሰቆቃ አገዛዝ በነጠላው በማወዳደር የተሻለ ሆኖ ለመታየት

*መታከትና 'የምንሰጥህ ይበቃሃል አርፈህ ተቀመጥ' ዓይነቱ ይዞታ አንድም ትዕቢታዊና ሕዝብን ከመናቅ የመነጨ አለያም ሕዝብ የሥልጣን ባለቤትና ምንጭ መሆኑን ካለማመንና ካለመቀበል የመነጨ እጅግ ኋላ-ቀር አምባ-ገነንነት ከመሆን አያልፍም፡፡ ሕዝብን ከመናቅ የበለጠ ደግሞ የድንቁርና ቁንጮ የለም፡፡ ሆኖም ግን የለየላቸው ምፀተኛ አምባ-ገነን አገዛዞች ሣይቀሩ ሕዝብን እየጨቆኑና ቁም-ስቅሉን እያሳዩም እንኳ የሚሠሩትን የጥፋት ሥራ ሁሉ በሕዝብ ስም ማድረጋቸው የታወቀ ነው፡፡*

*በተለይ ከግንቦት አሥራ-አምስት ሁለት-ሽህ-ሁለት ምርጫ-የለሽ ምርጫ ወዲኽ ከሞላ ጎደል የሁሉም ኢትዮጵያዊ ጥያቄ "ከዚኽ ወዴት?" የሚል ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ በገዥው ፓርቲ ሕወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎች ለመቶ-ፈሪ እጅ በሆነ ውጤት 'ምርጫው'ን አቸንፈናል ተብሎ በዜና ማሰራጫ አውታሮቻቸው አማካይነት መለፈፉ ብዙ ወገኖችን በጣም አስደንግጧል፣ በርካቶችን ከምር አስገርሟል፣ ከልብም አሣዝኗል፣ አንዳንዶችን አስጎፍቷል፣ የተወሰኑትን ተስፋ ወደ መቁረጥ እንዲያዘነብሉ ገፋፍቷል፣ ያላነሰ ቁጥር ያላቸውን ግብታዊ ምላሽ እንዲሰጡ አድርጓል፣ ጥቂቶችን ደግሞ ከሁሉ በፊት ረጋና ሰከን ብለው ጉዳዩን ከራሣቸው ጀምሮ ከሥር-መሠረት ለመመርመርና ቁርጠኛ ውሳኔ ለማድረግ እራሣቸውን እንዲያሳምኑ አድርጓል፣ በመኻሉ የጉዳዩ ባለቤት የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ስሜቱን በምሬትና በቁጭት አምቆ ሁሉንም የዚኽን ድኅረ-ምርጫ ትዕይንት ተዋንያን በትዝብትና በትዕግስት መመልከቱን ቀጥሏል፡፡*

*በኢሕአዴግአውያን በኩል ከጥሬ ድንጋጤና ግራ መጋባት እስከ ደመ-ነፍስ ደስታ፣ ከጭፍን ትዕቢት እስከ ምፀት የተሞላው ድንፋታ ሲንፀባረቅ ተስተውሏል፡፡ በመሪዎቹ በኩል ጊዜ ሳያባክኑ "ለአዲሱ እውነታና ክስተት" የሚመጥን ስልታቸውን ቀይሰው፣ አሰላለፋቸውን አስተካክለውና ንጥጥራቸውን አሹረው በምርጫ ሳቢያ "ያገኙትን" የበላይነት ለማጠናከር በሙሉ ኃይላቸው በመንቀሳቀስ ላይ ናቸው፡፡ የዚኽ አዲስ ዙር የሕዝብ ትግል ቅልበሳ እርምጃም ዋናው ዓላማ የለውጥ ኃይሉ መልሶ እንዳያንሠራራ መደቆስና ሙሉ ቁጥጥር ሥር በማዋል ሕዝባችን እንበለ-አማራጭ እንዲቀር ማድረግ ነው፡፡ የመጀመሪያ እርምጃቸው አባላቱንና ደጋፊዎችን "መሥመር ማስያዝ"፣ ሁለተኛው የሕዝብን ቁጣ በልዩ ልዩ ዘዴዎች ማፈን፣ ማረጋጋትና ግራ ማጋባት፣ ሦስተኛ በውጭ የሚገኘውን ኢትዮጵያዊ መበተንና እስካሁን ቀጥ ብሎ የዘለቀውና ለአገዛዙ የልብ ውጋት ሆኖ የቆየው የተቃውሞ ድምፃቸውን ቦታ ለማሳጣት ጥረት ማድረግ፣ አራተኛው የዓለም-አቀፍ ኅብረተሰቡን ቅሬታ ማለዘብና የመነመነ አመኔታን ማደስ፣ አምስተኛ ገና አስቀድሞ ቅድመ-ምርጫ ሂደት ላይ የቤት ሥራ የሠራበትን ተቃዋሚውን እርባና-ቢስ የማድረግና የመበተን ተግባር ማጠናከር፣ መልሶ እንዳይቋቋም ማዋከብና አባላትና ደጋፊዎች ተስፋ እንዲቆርጡ ውዥንብር ማናፈስ፣ እና ስድስተኛና መጨረሻ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሌላ ምንም አማራጭ እንዳይኖረው በሚያደርግ መልክ እራስን እስከ-ወዲያኛው ማደላደል ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ ለእነዚኽ እቅዶቻቸው ተግባራዊነትም የረቀቁ ስልቶችን ከመጠቀም ጀምሮ እስከ አዳዲስ ምልምሎችና የቆዩ ወዶ-ገቦችን እንደ ተናካሽ ውሻ በማሰለፍ ተግተው ይሠራሉ፡፡ በተለይ ስለ ልማትና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅሞች ጉዳይ የአጠቃላይ እንቃቃሴው አዝማች ሆነው ጧት ማታ ይለፈፍላቸዋል፡፡ አገዛዙ ታዲያ እነዚኽን እቅዶች በተግባር ለመተርጎም አቅሙና ፍላጎቱ እንዳለው ግልፅ መሆኑ ብቻ ሣይሆን ሁኔታዎች ደግሞ አመቺ ሆነውለታል፡፡ ከሁሉም ከሁሉም ሁኔታውን ያመቻቸለት ከማንምና ከምንም በላይ ደግሞ እስካሁን ብሔራዊ አማራጭ ሆኖ ለመቅረብ አቀበት የሆነበት ኢሕአዴግን ተፃርሮ የቆመው ወገን ነው ማለት ይቻላል፡፡ በተለምዶ 'ተቃዋሚው ክፍል' እየተባለ የሚጠራው ይኽ ጎራ ለጊዜው ከመቸውም ይበልጥ ስብጥርጥሩ ወጥቶ መገኘቱ የአደባባይ ምሥጢር ነው፡፡ ይኽ ሁሉ እንደሚደርስ ደግሞ ይኽ ክፍል ከምርጫ ዘጠና-ሰባት ማግስት ጀምሮ የተከተላቸው ሂደቶች ቀጥተኛ አስተዋጽዖ እንዳላቸው አሌ የሚባል አይደለም፡፡ ይሁንናም ሁኔታውን መልክ ለማስያዝ በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጭ ሊደገፉ የሚገባ የሰከኑ ሙከራዎች አለመቋረጣቸውና መቀጠላቸው አበረታች ነው፡፡ ሁኔታውም ለሰከኑና በደንብ ለተጠኑ እንቅስቃሴዎች አመቺ ነው፡፡*

*በሁለቱ ኃይሎች ማለትም በገዥው ክፍል (ፓርቲ) እና በተፃራሪው በኩል በሚደረገው ለሕዝብና ለአገር የተሻለ ሁኔታን ለመፍጠር አማራጭ ሆነ ለመገኘት 'የተለወጥ-አልለወጥም' ፍልሚያ ከሞላ-ጎደል ቋሚ ነው በሚያሰኝ ደረጃ ሳይዛነፍ የቀጠለና የሚታይ ልዩነት አለ፤ ይኸውም ገዥው ክፍል ከራሱ ስህተት ብቻ ሣይሆን ተቃዋሚው ወገን ከሚሠራቸው ስህተቶች ቶሎ ይማራል፣ የፍልሚያውን ትልም (አጀንዳ) ለመቆጣጠርና ከእጁ እንዳይወጣም ይጥራል፡፡ በአኳያው ለለውጥ የቆመው ኃይል ከስህተቱ አለመማር ብቻ ሣይሆን አዳዲስ ዙር ስህተቶችንና ግድፈቶችን በራሱ ላይ እየቆለለና እራሱን በነሱ እየተበተበ እነሱን ለማረምና ለማስተካከል ጊዜውን ስለሚያባክን ቅድሚያን*

ይለቃል፣ የትግል አጀንዳውንም መቆጣጠር ያዳግተዋል። በመሆኑም ትግሉ ከተከላካይነት (ከተከላካይነትም ጥንካሬና ስልት የጎደለው አንካሳ ተከላይነት) ሊወጣ ያዳገተው ስለሚሆን ሌላው ቀርቶ አገዛዙ እራሱ የሚያደርጋቸውን ጉልህ የሆኑ ስህተቶች በተገቢ ለመጠቀም ያቅተዋል፤ በአጭሩ የትግል መሥመሩንና ንጥጥሩን (አጀንዳውን) ቁጥጥርና ቅድሚያን ይለቃል። እንግዲህ የኢትዮጵያን ሕዝብ የሥልጣኑ ባለቤት ለሚያደርግ ሕገ-መንግሥታዊ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እውን መሆን የሚደረገው ትግል ችግር ያለው እዚኽ ላይ ነው።

ይኽ ጥንውት ደግሞ በኢትዮጵያ ለውጥ እንዲመጣ የሚታገለው ወገን እንዲሁ በደፈናውና በግልቡ ፈልጎ ያመጣው ሆኖ ወይም የግድ የመሪዎቹ ብቻ ስህተት ተደርጎ መወሰድ ያለበት አይመስለኝም። በፖለቲካው መስክ የተሰማራውና ለለውጥ የቆመው ክፍል በአገሪቱ ያለው አጠቃላይ የፖለቲካ ሁኔታ ውልድና ነፀብራቅ መሆኑ ግልፅ ነው። ይኽ አጠቃላይ የፖለቲካ ሁኔታ ደግሞ በድርጅቶች አደረጃጀትም ሆነ አሠላለፍ፣ አሠራርም ሆነ ይዞታ ላይ ቀጥተኛ አስተዋጽዖ አለው። በአኳያው ይኽን ሁኔታ በመፍጠሩና በማስኬዱ ረገድ ገዥው ፓርቲ/መንግሥት ዓብይ ሚና ሲኖረው፣ ሁኔታው እንዳይቀጥል በማድረጉ በኩል ግን ለለውጥ የቆመው ኃይል ተልዕኮ እንደሚሆን መታወቅ ይኖርበታል። በጥቅል አቀራረብ ለአዎንታዊ ለውጥ የቆመው የአገሪቱ የፖለቲካ ክፍል ማለት አገር-ወዳድና ዴሞክራት ኃይሉ መሠረታዊ ችግሮች አሉበት። እነኝኽ የለውጥ ኃይሉን ተብትበው የያዙ ችግሮችም ይኽ ክፍል ሊለውጠው የሚታገለውን ሥርዓትና የአራማጁን ኃይል ተፈጥሮአዊ ባኅሪ ከሚከተለው መሠረታዊ ርዕዮት (ፍልሥፍና) እና በመስክ ላይ ከሚታየው እውነታ በቅጡ የተገናዘበና መጣኝ ፍልሥፍና፣ አደረጃጀት፣ አወቃቀርና አሠራር መከተል ያለመቻልን በሚያኽል ከባድ የስትራቴጂ ዝንፈት የተጠቀለሉ ሆነው እናገኛቸዋለን።

መቸም ቢሆን ቢያንስ ላለፉት ወደ አራት ለሚጠጉ አሥርተ-ዓመታት የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ በተለይም ወጣቱ ክፍል፣ በተደራጀ መልክ አገሩንና ሕዝቧን ከቀጣይ ሰቆቃ ለመታደግና ሰብዓዊ መብቶች እንዲከበሩ፣ ፍትኅና እኩልነት እንዲሰፍኑ፣ አሣፋሪ ድህነትና ችግር አክትመው ልማትና እድገት እውን እንዲሆኑ እና የአገራችን አንድነት እንዲከበር ያልከፈለው መስዋዕትነት የለም። ግን የተከፈለውን መስዋዕትነት የሚመጥን ውጤት አለመገኘቱ ደግም በአገሪቱ አሁንም የቀጠለው አሣፋሪ የረሃብ አዙሪት፣ የሚታየው አስነዋሪ የሰብዓዊ መብት ጥሰት፣ በኀዘኔታ የምናየው የዜጎች ተስፋ መጫጨትና በዚኽም ምክንያት ለሕይዎታቸው እንኳ ዋስትና በሌለው አደገኛ ሁኔታ አገራቸውን ጥለው ለመሰደድ የሚያደርጉት መራኮት፣ ወዘተ.. ሁሉ የማይካዱ፣ አፍጥጠውና አግጥጠው ያሉ ሊለባበሱና አሌ ሊባሉ የማይችሉ አስረጅዎች መኖራቸው እውነታውን ያረጋግጣል። ችግሮቻችን በርካታ ብቻ ሣይሆኑ መሠረታዊና ሥር የሰደዱ ናቸው። እነኝኽ ችግሮች ሰው-ሰራሽ በተለይ ሕዝብ የመብቱ ሙሉ ባለቤት መሆን ካለመቻሉ የተነሣ ከተፈጠረ የመልካም አስተዳደር እጦት ውልድ መሆናቸው ግልፅ ነው። ስለሆነም ከአፄ ሰብታኅ ጀምሮ በብዙ ሽዎች ለሚቆጠሩ ዓመታት ያልተቋረጠ ቀጣይ የመንግሥት ሥርዓት ያለውና በብዙ ያላባሩ ፈተናዎች ውስጥ ያለፈ፣ ሠርቶና ጥሮ-ግሮ ችግሩን ለመቋቋምና እራሱን ለማሻሻል ብቃቱ፣ ፍላጎቱና ችሎታው ያለው ሠፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሥልጣን ብቸኛ ምንጭና ባለቤት መሆኑ በተግባር ቢረጋገጥለት፣ የመብቶቹ ባለቤት ቢሆን፣ ሁኔታዎች ቢመቻቹለትና ከግልና ከቡድን ጥቅም በላይ ሕዝብንና አገርን የሚያስቀድም አመራር ቢያገኝ፣ ችግሮቹን በብቃትና በአጭር ጊዜ መወጣት ብቻ ሣይሆን ተፈጥሮ የለገሰችውን ትሩፋት በአግባቡ ተጠቅሞ አገራችንን የተረጋጋች፣ የበለፀገችና ለሌሎች አገሮች ጥሩ ተምሳሌትና አርኣያ የምትሆን እንደሚያደርጋት ፈጽሞ አልጠራጠርም።

ታዲያ የኢትዮጵያን ሕዝብ የሥልጣኑ ባለቤት የሚያደርግ ሁኔታ ችግሮቻችንን በአስተማማኝ ለመፍታት አስፈላጊ ከሆነ ያንን እንዴት እውን ማድረግ ይቻላል? በዚኽ ረገድና ከዚኽ አኳያ ኢትዮጵያውያን በአጠቃላይ እና በተለይ ገዥው ፓርቲ እና ለአዎንታዊ ለውጥ የቆመው አገር-ወዳድና ዴሞክራት ኃይል ሚናና ታሪካዊ ኃላፊነት ምን ይሆናል? ከዚኽ ሁሉ በፊት ደግሞ ዴሞክራትና አገር-ወዳዱ ኃይል አሁን ከሚገኝበት አንገት-አስደፊ ሁኔታ እንዴት መላቀቅ (መውጣት) እና ሁነኛ ብሔራዊ አማራጭ መሆን ይችላል? ለሚሉት ጥያቄዎች ግልፅ ምላሽ ሊሰጥበት ይገባል እላለሁ። ስለሆነም እነዚኽንና ሌሎች ተዛማች ጥያቄዎችን ህሳቦት ውስጥ ባስገባ መልኩ ጉዳዩን በአጥፊና-ጠፊነት አስተሳሰብ ሣይሆን በአንዲት አገር ውስጥ ሁሉም ተጋሪ-አቸናፊ ለሚሆንበትና የዜጎች እኩልነትና ፍትኅ የሚረጋገጡበት ሥርዓት እውን እንዲሆን ከሚደረገው የጋራ ሕዝባዊ ትግላችን አኳያ በመቃኘት የግል አስተያየቴን በተከታታይ ለማቅረብ እሞክራለሁ።

***በክፍል ሁለት ይቀጥላል...***